**ይድረስ ለተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ**

# የግል ሚዲያው ከህግ በላይ ሲሆን ዝም ተብሎ መታየት አለበትን?

**ታሪኩ ዘርይሁን** 08-20-14

ለዛሬው ፅሑፌ መነሻ የሆነኝ የተከበሩ የፓርላማ አባልና የአንድነት ፓርቲ ተወካይ አቶ ግርማ ሰይፉ ሰሞኑን "ፋክት" በተሰኘው መፅሔት ላይ "የግል ሚዲያዎች ክስ–ለምን?" በሚል ርዕስ ያቀረቡት አራምባና ቆቦ የሚረግጥ ፅሑፍ ነው። አቶ ግርማ በፅሑፋቸው ላይ መንግስት እንዴት ጋዜጠኞችን እንደሚያስር ለማስረዳት በመጋቢት 1999 ዓ.ም የወጣውን "የዴሞክራሲ ሰርአት ግንባታ ትግልና አብዮታዊ ዲሞክራሲ" በተባለ ሰነድ ላይ መመስረታቸውን ይገልፃሉ። እኔም "ሰውዬው ምን እያሉ ነው?" የሚል ጥያቄን በማንሳት ምላሽ ይሆነኝ ዘንድ ሰነዱን ከሰዎች አጠያይቄ አገኘሁት። አነበብኩት። የአንድነቱን ሰውዬ ፅሑፍንም ደግሜ አየሁት።…በአያሌው ተገረምኩ። እናም ሰውዬው ሰነዱን እንዳሻቸው ከመተርጎም ባለፈ፤ የሚዲያ ስራ እንዴት እንደሚከናወን ጥቂት ግንዛቤ እንኳን ሳይኖራቸው በለመደባቸው ሁሉንም ነገር የመቃወም አባዜ ያሻቸውን ለማለት እንደፈለጉ ለመገንዘብ ጊዜ አልወሰደብኝም።…

…እርግጥ አቶ ግርማ ህገ-መንግስቱ በሰጣቸው መብት በፅሑፍም ሆነ በቃል የፈለጉትን ማለት መብታቸው ነው። ግን…ግን የሚባለው ነገር ከዕውነታው ያልራቀ፣ ስሜታዊ ያልሆነና 'ለመቃወም ብቻ መቃወም' ከሚለው የሀገራችን ተቃዋሚዎች የተለመደ ቀኖና ወጣ ማለት ይኖርበታል። አንድ "ፀሐፊ ነኝ" የሚል ሰው በቅድሚያ ስለሚፅፈው ነገር ራሱ በደንብ ማወቅ ይኖርበታል። ሲቀጥልም የሚሰጠው ትንታኔ በጉዳዩ ዕውነታ ላይ ተመርኩዞ እንጂ፤ ወረቀትና ብዕር ስላገኘ ብቻ ውስጡ ያለውን ስሜት እያነበበ ለሌላው ያልተገባ ምስል ለመስጠት መጣር የለበትም። እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ አንባቢን የሚያሳስት ከመሆኑም ሌላ፤ "ፀሐፊውን" ግምት ላይ መጣሉ አይቀርም።…ታዲያ በእኔ እምነት አቶ ግርማ የጠቀሱትን ሰነድ ለመተንተንና እርሳቸው እንዳሉት 'ሰነዱን ያላገኙ ሰዎች አውቀው እንዲረዱት' የማድረግ ዕውቀቱ፣ ክህሎቱ፣ ብቃቱና እምነቱ የላቸውም።

የተከበሩ የፓርላማውን አባል በተለይም ከምርጫ 2002 ወዲህ በኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልነታቸው በደንብ አውቃቸዋለሁ። ፓርላማ እንደገቡ በመንገድ ላይ በአጠና ተናራችነቱ፣ ነጥብ ያዥ በሌለበት ተቧቃሽነቱ፣ ከአምሳያዎቹ ጋር ሲጣመር "ከእኔ ወዲያ ላሳር" ባይነቱ፣ አንዱ ሌላውን በሚዲያ ላይ ተሳዳቢነቱ፣ ሽብርተኞችንና በሽብር የሚጠረጠሩ ግለሰቦችን አቅፎ ያዥነቱ እንዲሁም አመራሮቹ ሰሞኑን በስልጣን ጥማት ምክንያት ገመናቸውን ለአደባባይ በመዝራት የተበታተኑበቱ የአንድነት ፓርቲን ጥያቄም ይሁን ሃሳብ እንደ መፅሐፍ ቅዱስ ሳይጨምሩና ሳይቀንሱ አቀርቅረቅ ያነበንቡ እንደነበር አስታውሳለሁ። በፓርቲው መራጮች የማስተዛዘኛ ድምፅ እንኳን ባያገኙም፤ ከአቀርቅሮ አንባቢነት ወደ ፓርቲው ሊቀመንበርነት ውድድር ሲያመሩም አይቻቸዋለሁ–ሰውዬውን። ምን ይህ ብቻ። ከአቀርቅሮ አንባቢነት በአንዴ ወደ መፅሐፍና መጣጥፍ ፀሐፊነት ብሎም ወደ ቋሚ አምደኛነት ሲቀየሩ በዓይኔ በብሌኑ ተመልክቻቸዋለሁ።…በእኔ እምነት ይህ ወደ ብርሃን ፍጥነት የቀረበው የአቶ ግርማ "የአጭር ርቀት ሩጫ"፤ አንድነት ፓርቲ ውስጥ ካለው ጭፍን ጥላቻ ጋር ተዳምሮ፤ ሰውዬው በዕውቀት፣ በሃቅና በምክንያታዊነት ላይ የተመሰረተ ነገር ሊፅፉ አይችሉም። ለዚህ ደግሞ ዋነኛ ማሳያው ቀደም ሲል በመግቢያዬ ላይ የጠቀስኩት ፅሑፋቸው ነውና ወደዚያው ላምራ።…

አቶ ግርማ ጥሩ "ጠቃሽ" ናቸው–የተባለውን ነገር በአግባቡ አይረዱትም አሊያም ሆን ብለው ያጣምሙታል እንጂ። እርሳቸው በጠቀሱት "የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ትግልና አብዮታዊ ዲሞክራሲ" ሰነድ ላይ፤ "ሚዲያው በነፃነትና በጤናማ አኳኋን እንዲያድግ ማድረግ ለማንም ሲባል የሚሰራ ስራ ሳይሆን በአገራችን የዴሞክራሲ ስርአትን እውን ለማድረግ ተብሎ የሚከናወን በመሆኑ ለሌሎች የዴሞክራሲ ሰርአት ግንባታ ስራዎች ከምንሰጠው ትኩረት የማይተናነስ ትኩረት ለዚህም ስራ መሰጠት አለበት" የሚል አባባል ሰፍሯል፡፡ ታዲያ ሰውዬው የጠቀሱትን ይህን አባባል፤ ከጥሬው ትርጉሙ በዘለለ "ምን ዓይነት ነፃነት ፣ምን ዓይነት ጤናማነት?" የሚል ጥያቄን በማንሳት፤ መልሰው ራሳቸው ምላሽ ሲሰጡ እንመለከታለን–"ኢህአዴግ ሌሎችንም የዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ማለትም የብዙኃን ማኅበራትን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ የህዝብ ምክር ቤቶች እንዲሁም የዳኝነት ስርዓቱን ምን ያህል ነፃነት እየከለከለ ጤና እንደሚነሳቸው ስንረዳ፣ ምን ዓይነት ነፃነትና ጤና እንደታዘዘልንም መረዳት ቀላል ነው" በማለት። እንግዲህ ከዚህ የአቶ ግርማ አባባል የምንረዳው ነገር ቢኖር፤ ገዥው ፓርቲ ለሚዲያው ነፃነትና ጤና አልሰጠውም የሚል

የ"አላዋቂ ሳሚ…" እንጉርጉሮን ነው። ሃቁ ግን ያለ አንዳች ዕውቀት አቶ ግርማ እንደሰነዘሩት ድምዳሜ አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ መንግስት ራሱ እንዲፈጠር ያደረገውን የግል ሚዲያ መልሶ እንደ ተቃዋሚ የሚቆጥርበት አካሄድ አለ ብሎ ማመን በራሱ የሚያመላክው ነገር ቢኖር ሰውዬው መሰል አጀንዳ የሚያራምዱ የተቃውሞው ጎራ ባለሟሎችን ሃሳብ እያራገቡ መሆኑን ነው። ምክንያቱም በትንሹም ይሁን በትልቁ፣ በተገኘው ተባራሪ አጀንዳ ሁሉ እንዲህ ዓይነት ያልተገባ ስም በመለጠፍ የሚታወቁት እነርሱ በመሆናቸው ነው። አቶ ግርማ እዚያው ፓርላማ ውስጥ ሆነው ለማወቅ አይፈልጉ እንጂ፣ የኢፌዴሪ መንግስት በህገ-መንግስቱ ላይ በግልፅ የተደነገጉት ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብቶች እውን እንዲሆኑ ከመታገሉም በላይ እንዳይሸራረፉም በፅናት ታግሎላቸዋል፤ እየታገለላቸውም ነው። በተለይም በሰነዱ ላይ እንደተገለፀው ሚዲያ በሀገሪቱ የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ እመርታዎች ላይ የራሱን አሴት የሚጨምር መሳሪያ አድርጎ ነው የሚመለከተው፡፡ ይሁንና ሚዲያ ህግና ስርዓትን አክብሮ ካልተንቀሳቀሰ ከጠቀሜታው ባሻገር፤ በሁለንተናዊ የዕድገትና የዴሞክራሲ ባህል ግንባታ ዓላማዎች ላይ ጉዳት ሊያደረስ እንደሚችል ማወቅ ይገባል።

እርግጥ የኢትዮጵያ መንግስት የሚዲያን ጉዳት ለማስቀረት ሲል ጥቅሙን የመገደብ አካሄድ እንደማይከተል አቶ ግርማ ማወቅ ያለባቸው ይመስለኛል፡፡ እንደ ሌሎቹ የዴሞክራሲ ግንባታ ስራዎች ሁሉ፤ ሚዲያው ነፃና ጤነኛ ሆኖ እንዲያድግ ፈርጀ ብዙ ተግባራትን ማከናወኑንም መገንዘብ ከጭፍን ጥላቻ ያድናል፡፡ የቅርብ ጊዜውን ትውስታ ብናነሳ እንኳን ሚዲያ ለሀገራችን የዴሞክራሲ ግንባታ ጤነኛ በሆነ አኳኋን ሙያዊ ሃላፊነቱን እንዲወጣ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ 590/2000 ´ማውጣቱን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ታዲያ በሰነዱ ላይ እንደተመለከተው መንግስት ሚዲያው ነፃና ጤነኛ በሆነ አኳኋን እንዲያድግና እንዲመነደግ የሚያደርጉ ስራዎችን የሚፈፀመው ለማንም ብሎ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ተግባሩን የሚከውነው ከባህሪው በመነጨ፣ በሀገራችን ውስጥ በመገንባት ላይ የሚገኘው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲያብብና ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ካለው ፅኑ ፍላጎት ተነስቶ የሚከወን ዴሞክራሲያዊ ተግባር በመሆኑ ነው፡፡

እዚህ ላይ ግን አቶ ግርማ እንዲገነዘቡት የምሻው ጉዳይ፤ በየትኛውም ሀገር ሚዲያ እንደ ማንኛውም የሙያ ዘርፍ የሥራ ነፃነት ስላለው ብቻ የሀገሪቱን ህግና አሰራርን እንዲሁም

የራሱን የስነ-ምግባር ደንብ እየደፈጠጠ እንዳሻው ሲፈነጭ ዝም ተብሎ የሚታይ አለመሆኑን ነው። እናም አንዳንድ የግል ሚዲያዎች ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን ከጀርባ በጦር ለመውጋት ሲፈልጉ፣ የሚዲያ ነፃነትን ጭንብል ተሸፋፍነው ወንጀል ለመስራት ሲሞክሩ እንዲሁም ህግና ስርዓትን ደፍቀው በማን አለብኝነት የያዙትን ቀለምና ወረቀት እስኪጨርሱ ድረስ እየለቀለቁ ተጠያቂነት በሌለው አኳኋን በአሉባልታ ላይ የተመሰረቱና የተዛቡ ዘገባዎችን ለህዝብ ሲያቀርቡ ብሎም የፀረ ሰላም ሃይሎችንና የአሸባሪዎችን አጀንዳ ሲያራግቡ የሚዲያውን ጤናማነት በሚቆጣጠሩት የሀገሪቱ ህጎች መጠየቃቸው የሚቀር አይመስለኝም፡፡ ለምን ቢባል፤ በማንኛውም ዴሞክራሲያዊ ሀገር ውስጥ የህግ የበላይነት ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ ባለመሆኑ፣ በሚዲያ ውስጥም የሚሰራ ሆነም ማንኛውም ሰው ህጋዊ አሰራሮችን ተላልፎ ሲገኝ በህግ አግባብ የሚጠየቅ በመሆኑ ነው። እናም የተከበሩ የፋክት “ፀሐፊው” በሰነዱ ላይ ሚዲያው “ነፃና ጤናማ” ተብሎ የተገለፀውን ዕውነታ ከዚህ አኳያ ቢረዱት ማለፊያ ይመስለኛል።

በእኔ እምነትና አቶ ግርማም ከሰነዱ እንደጠቀሱት፤ መንግስት የዳበረ ዴሞክራሲን ለመገንባት የግሉ ሚዲያ ወሳኝ መሆኑን የሚገነዘብ ይመስለኛል። እንደ አንድ የዴሞክራሲ ማሳለጫ ተቋም ሆኖ እንዲያድግም ይሻል። በመሆኑም በሀገራችን የዳበሩ የመንግስት (የህዝብ) እና የግል ሚዲያዎች እንዲኖሩ መፈለጉ አይቀሬ ነው። ይህም በህገ-መንግስቱ ላይ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን ተግባራዊ ከማድረግ የመነጨ ነው። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ይህ የመንግስት ቁርጠኛ አቋም የግልና የመንግስት ሚዲያዎች ስራቸውን በነፃነትና በጤናማ ህጋዊ መንገድ የሚያከናውኑበትን የተስተካከለ ምህዳር በመፍጠር ላይ ብቻ የያጠነጠነ አይመስለኝም። ከዚህም በላይ ረጅም ርቀት ሄዶ ሚዲያውን ለመደገፍና ለማጠናከር ጭምር ያለመ ነው።

ታዲያ እዚህ ላይ አቶ ግርማ ማወቅ የሚገባቸው ሃቅ ያለ ይመስለኛል። ይኸውም ሚዲያው በነፃነትና በጤናማ አኳኋን እንዲያድግ ለማድረግ የሚከናወኑት ስራዎች ‘እገሌን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት’ ተብለው የሚወጠኑ አለመሆናቸውን ነው። ይልቁንም የሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባህል ግንባታ እንዲጎለብት ከሌሎች የዴሞክራሲያዊ ግንባታ ስራዎች ባልተናነሰ መልኩ ሚዲያም የበኩሉን አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ስለሚታመንበት ይመስለኛል። መቼም አቶ ግርማ ምንም እንኳን ከዴሞክራሲ እሳቤዎች ጋር ጠበኛ የሆነው የአንድነት ፓርቲ አባል ቢሆኑም፤ ለአፋቸውም ቢሆን “ለምን የሀገራችንን ዴሞክራሲ

እናጠናክራለን?” ሊሉ አይችሉምና ቀደም ሲል ‘ሚዲያው ነፃና ጤናማ ሆኖ እንዳያድግ መንግስት ይፈልጋል’ በሚል ሰነዱን ሆን ብለው በማጣመም፣ ይባስ ብለውም ያለ አቅማቸው በመተንተን ወደ ተሳሳተ ዕይታ ይስቡታል የሚል ዕምነት አለኝ። የተከበሩ አቶ ግርማ ሆይ! እርግጥ ከልብዎ የግሉ ሚዲያ እንዲዳብርና እንዲፋፋ የሚፈልጉ ከሆነ እርስዎ ራስዎ “በአምደኝነት” ሳምንታዊ ደቦ ገብተው የሚፅፉበትንና ከስያሜው ጋር የማይገናኘውን “ፋክት” የተሰኘውን የሚርተኞች ስብስብ መፅሔትን ዞር ብለው ሊያጤኑት የሚገባ ይመስለኛል።

ምንም እንኳን በሚያስገርም ሁኔታ ለህዝብ እየሰራ ያለውን ገዥውን ፓርቲ በፅሑፍዎ ላይ “ኢህአዴግ ህዝብ፣ ህዝብ እያለ ያላግጣል” ቢሉም፤ እርስዎም ቢያንስ ህዝብ የመረጥዎት የፓርላማ አባል እንደመሆንዎ መጠን፤ ሚዲያው ነፃና ጤናማ ሆኖ እንዲሁም ከስሜታዊነት፣ ከአሉባልተኝነትና ከጭፍን ጥላቻ ርቆ ብሎም እንደማንኛውም ሀገር ሚዲያ የሀገሩን ህጋዊ አሰራሮችን አክብሮ ተግባሩን እንዲያከናውን የማስተካከል ሃላፊነት ያለብዎት ይመስለኛል። እርስዎ ለሙያው እምብዛም ቅርብ ባይሆኑም ጋዜጠኝነት ህዝብን የሚያስተምርና የሚያሳውቅ ሙያ መሆኑን ሳይሰሙ ይቀራሉ ብዬ አልገምትም። በመሆኑም ለያውቁት የሚገባው ጉዳይ ሙያው “እዚህ ጋ ጥሩ ተሰርቷል፣ እዚህ ጋ ደግሞ መስተካከል ያለበት ጉዳይ አለ” እያለ ተግባሩን ሳይወጣ ቀርቶ፤ በአንፃሩ በፍፁም ጥላቻ ላይ ተመርኩዞ ሁልጊዜ ፅንፈኛ አስተሳሰቦችን ብቻ የሚያራምድ ከሆነ ህዝብን ከማደናገር ውጪ ሃላፊነቱን ተወጥቷል ሊባል አለመቻሉን ነው።

ሚዲያ የህዝብን አስተያየት የሚያስተናግድ፣ የውይይት መድረክ ሆኖ የሚያገለግልና ህግና ስርዓትን አክብሮ የሚሰራ ተቋም እንጂ፤ ልክ እርስዎ እንደሚፅፉበት “ፋክት” መፅሔት የጥላቻ ስሜት መጋለቢያ ፈረስ ከሆነ ጤናማ ነው ሊባል አይችልም። የዘገባው ዕይታ የተንሸዋረረ ሊሆን ስለሚችልም ሚዛናዊነትን በመሳት አሉባልታዊ ድርሳኖችን እያተመ ለማውጣት ይገደዳል። ከፍ ሲልም የአንዳንድ ፀረ-ሰላም ሃይሎችን አጀንዳ የራሱ አድርጎ በማቅረብ የጎላ ስህተት ሊፈፅም ይችላል። በዚህም በኪራይ ሰብሳቢነት ተተብትቦ በራሱ እጅ ነፃነቱን አሳልፎ ይሸጣል።

እርግጥ ይህ ዕወነታ አቶ ግርማ ሰነዱን ዋቢ በማድረግ “የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካ ኢኮኖሚ በልማታዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በተሟላ መልኩ መተካት አለበት” ወደሚለውና “ከዚህ በኋላ ኪራይ ስብሳቢ ሚዲያ ሲባል አቤት ማለት ይኖርብናል” (“ፋክትን” ማለታቸው

ይመስለኛል) ሲሉ ራሳቸው በራሳቸው ላይ ብያኔ ወደሰጡበት ጉዳይ ይወስደናል። ለነገሩ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ "የዜሮ ድምር ጨዋታ" የሆነው የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር መሰበሩ የግድ ነው። ምንም እንኳን አቶ ግርማ ከሚከተሉት የፓርቲያቸው ርዕዮተ-ዓለም ተነስተው በሰነዱ ላይ "ኪራይ ሰብሳቢ" በሚል የተገለፀበትን አግባብ በፅሑፋቸው ላይ እየደጋገሙ ለመኮነን ቢሞክሩም፤ እሳቤያቸው ግን ያው የተለመደው የማጥላላት ዘፈን ከመሆን የሚዘል አይመስለኝም። ምክንያቱም ሚደያ እንደ ሀገራችን ያሉ በማደግ ላይ የሚገኙ ሀገሮች ህዝቦችን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ሁነቶችን የማስታወቅ፣ የማስተማርና የማነሳሳት ተግባራትን ማንገብ ስላለበት ነው። እነዚህ ህዝቦች ካሉበት የድህነት አዙሪት ቀለበት ነፃ እንዲሆኑና በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉ ሚዲያው የበኩሉን ሚና ማበርከት ይኖርበታል።

ህዝብን ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ለማላቀቅ፣ ፈጣን ሀገራዊ ለውጥን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ትክክለኛ የልማት ሃሳቦችን ህዝቡ እንዲገነዘባቸው፣ እንዲያምንባቸውና በአተገባበራቸውም በንቃት እንዲሳተፍ የሚያደርግ እንዲሁም አዎንታዊ የልማትና የዴሞክራሲ የለውጥ እሴትንም መገንባት አለበት። ታዲያ ይህን ሀገራዊ ሃላፊነት ለመወጣት ቀደም ሲል ከጠቀስኳቸው የኪራይ ሰብሳቢነትና የፖስተኝነት ተግባሩ ሊታቀብ ይገባል ባይ ነኝ። እናም እኔ እስሚገባኝ ድረስ አቶ ግርማ ራሳቸው እንዳሉት "ኪራይ ሰብሳቢ ሚዲያ" ሲባል "አቤት" ከሚሉ ይልቅ፤ እንደ ፓርላማ አባልነታቸው ይህ ሀገራዊ ራዕይ ዕውን እንዲሆን በሚደረገው ርብርብ ከ"ጎራው" ራሳቸውን ቢነጥሉ ብቻ በቂ ይመስለኛል። ኪራይ ሰብሳቢ ሲባል እጅ ማውጣት እንኳንስ ከእርሳቸው ቀርቶ እንደ እኔ ካለው ተራ ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር አይደለምና።

የተከበሩ የፓርላማ አባል በፅሑፋቸው ላይ ያነሱት ሌላኛው ነጥብ፤ በሰነዱ ውስጥ "የሚዲያ አውታሮች ገቢና ወጪያቸውን በትክክል እንዲያስመዘግቡና በየጊዜውም ጥብቅ ቁጥጥር እንዲደረግበት ማድረግ ወሳኝ ጉዳይ ነው" መባሉ አግባብነት የለውም የሚል ነው፡፡ ለዚህም "መንግስት በግል ሚዲያው ላይ ማስረጃ ሲያጥረው በቴሌቪዥን አንዳንድ ለሆዳቸው ያደሩ ሹሞችንና ባለሙያዎችን ሰብስቦ ከሚያትሙት አርባ አምስት ሺ፣ ሁለት ሺውን ብቻ ነው የሚሸጡት እያስባለ ፕሮፖጋንዳ ለመስራት ይዳክራል።..." በማለት መፅሔቶቹ ምንም ዓይነት ጥፋት እንደሌለባቸው ለመግለፅ ሞክረዋል። ማስረጃቸው ምን እንደሆነ ባላውቅም። ይሁንና አቶ ግርማ ስለ ሚዲያ አሰራር በቂ ዕውቀት ስለሌላቸው ነው

እንጂ፤ በየትኛውም ሀገር ውስጥ የሚገኝ ሚዲያ እንደ ማንኛውም ተቋም ገቢና ወጪው በትክክል ይመዘገባል፤ ጥብቅ ቁጥጥርም ይደረግበታል። ምክንያቱ ደግሞ ግልፅ ነው። ይኸውም ሚዲያ በባህሪው በአንድ ሀገር የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ዕመርታዎች ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሚና ሊጫወት ስለሚችል ነው። አቶ ግርማ በደንብ ይገነዘቡት ዘንድ ሩዋንዳ ውስጥ "ሬድዮ ፍራንስ ኮሊንስ" የተባለ ጣቢያ በሁቱና ቱትሲ ግጭት ወቅት ፈረንጆች እንደሚሉት "adding fuel into the fire" (በእሳት ላይ ቤንዚን የመጨመር) ተግባርን በመከወን በዚያች ሀገር ውስጥ ከ800 ሺ በላይ ሰዎች ለህልፈተ-ህይወት እንዲዳረጉ የበኩሉን ዘግናኝ ሚና ተጫውቷል። በመሆኑም እንዲህ ዓይነቱ አስከፊ ተግባር በሚዲያ አማካኝነት እንዳይከናወን ቁጥጥር መደረጉና የራሳቸው ዓላማ ያላቸው ፀረ-ሰላም ሃይሎችን ሚዲያውን ለእኩይ ፍላጎታቸው እንዳይጠቀሙበት ገቢና ወጪያቸው እንዲታወቅ መደረጉ ከቶ ጥፋቱ ምን ይሆን?... አቶ ግርማ በቴሌቪዥን ቀርበው ሙያዊ አስተያየታቸውንና እምነታቸውን የገለፁ ግለሰቦችን "ለሆዳቸው ያደሩ ባለሙያዎችና ሹሞች" እያሉ መዝለፍዎስ ተገቢ ነውን?... ምናለበት "አላዋቂ ሳሚ..." እንደሚሉት ዓይነት ባይሆኑ?...

እኔ እስከሚገባኝ ድረስ በኤሌክትሮኒክም ሆነ በህትመት ሚዲያው ላይ አንድን ጉዳይ እንዲያብራሩ የሚቀርቡ ግለሰቦች ወይም ተጠያቂዎች (Interviewee) ከሙያው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ግለሰቦች እንጂ፣ የተከበሩ የፓርላማ አባል እርሳቸውን በማይመጥን መልኩ እንደዘለፏቸው ዓይነት ሰዎች አይደሉም። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ነጋዴው ማህበረሰብ ስላለበት ችግር ማወያየት ከፈለገ፣ አቶ ግርማ ሰይፉ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል ("ነጋዴ" ከሆኑ ማለቴ ነው)። ታዲያ እርሳቸውም የነጋዴው ማህበረሰብ ያለበትን ችግር ሊያቀርቡ ይችላሉ–ጉዳዩ በቀጥታ ስለሚመለከታቸው። እናም በቴሌቪዥኑ ላይ መፅሔቶቹን አስመልክቶ አስተያየት ይሰጡ የነበሩት ግለሰቦች ከጉዳዩ ጋር በቀጥታ የዕለት ተዕለት ግንኙነት ያላቸውና ክንዋኔው እነርሱን የሚነካ መሆኑ በሚዲያው የሚታመንባቸው ሰዎች መሆናቸውን መገንዘብ ተገቢ ይመስለኛል– የተለመደና ሙያው የግድ የሚለው አሰራር ስለሆነ።

እናም እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ባለሙያዎቹ ያለ አንዳች ማስረጃ አንድን መፅሔት ከመሬት ተነስተው "እርባ አምስት ሺ አትሞ፣ ሽያጩ ሁለት ሺ ነው" ሊሉ አይችሉም። ምክንያቱም በጋዜጠኝነት ሙያዊ አሰራር ልክ እንደ ጋዜጠኛው ሁሉ፤ ተጠያቂው ባለሙያም በጉዳዩ

ላይ ጥናት አድርጎ መምጣት ስላለበት ነው– አድማጭ፣ ተመልካችና አንባቢ ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ይኖርበታልና። በመሆኑም ተጠያቂው ግለሰብ በደመ-ነፍስ የሚሰጠው ምንም ዓይነት ምላሽ ሊኖር እንደማይችል አቶ ግርማ ሊያውቁት ይገባል ባይ ነኝ። ለነገሩ አቶ ግርማ ስላልተገነዘቡት እንጂ አንድ መፅሔት አርባ አምስት ሺ ኮፒ አሳትሞ ሽያጩ ሁለት ሺ ብቻ ከሆነና የማስታወቂያ ገቢ ከሌለው የማሳተሚያ ገቢውን ከየት እንደሚያገኝ በቀላሉ ለመገመት አዳጋች አይሆንም።…

…እንዴት መሰልዎት!… ለአንድ ሚዲያ ህልውና መቀጠልና አለመቀጠል እንዲሁም ለጋዜጠኛው የስራ ዋስትና "የገቢ ምንጩ" ወሳኝ ድርሻ አለው፡፡ የገቢ ምንጩ ደግሞ ሁለት ናቸው– የማስታወቂያ ገቢና የአንባቢ ክፍያ። እናም መፅሔቱ ቀደም ሲል በባለሙያዎች ማስረጃ እንደተረጋገጠው አርባ አምስት ሺ አሳትሞ የሁለት ሺ የአንባቢ ክፍያ ብቻ የሚያገኝ እንዲሁም ያለምንም ማስታወቂያ የሚተዳደር ከሆነ ከየት አምጥቶ ያንን ሁሉ ኮፒ ሊያሳትም ይችላል?፣ የጋዜጠኞቹ፣ የቢሮና የሌሎች መጠቀሚያ ቁሳቁሶቹንስ ወጪ ከየት ሊያመጣ ይችላል?…መቼም አቶ ግርማ 'መፅሔቱ ላይ የሚሰሩት ግለሰቦች እንደ መፅሐፍ ቅዱሶቹ የሰማይ ወፎች ሁሉንም ነገር የሚያገኙት ከሰማይ መና ነው' ብለው የሚከራከሩኝ አይመስለኝም። እናም ያ መፅሔት ወይም ጋዜጣ የፋይናንስ ምንጩ ከወዴት እንደሆነ ከሚያነሳው የይዘት ጭብጥ በመነሳት የእነማንን አጀንዳ እያራገበ መሆኑን ለማወቅ ነብይ መሆንን አይጠይቅም፡፡

ይህም መፅሔቱ ወይም ጋዜጣው የአሸባሪዎችንና የፀረ-ሰላም ሃይሎችን የቴሌቪዥን ዲስኩር፣ የአክራሪ ሊዮ-ሊበራሊዝም አቀንቃኞችን ምኞታዊ ማላዘን ያለምንም የፊደል ግድፈት በካርቦን የገለበጠ ያህል ለሀገራችን አንባቢያን "እንካችሁ" በሚለው የአጀንዳ ቅብብሎሹ የሚታወቅ ነው። እኔን የገረመኝ ግን የተከበሩ አቶ ግርማ በየትኛው ጥናታቸው እንዳረጋገጡት ባይነግሩንም በደፈናው መንግስትን ለመቃወም ሲሉ ብቻ መፅሔቶቹ ህዝብ ተሻምቶ እንደሚገዛቸው ያለ አንዳች ሃፍረት ለመናገር መሞከራቸው ነው–ለዚያውም ህዝቡ የሚገዛው በመፅሐፍ ዋጋ ነው የሚል የተለመደ ቅጥፈትን በማከል።

እኔ ሆንኩ አቶ ግርማ እስከምናውቀው ድረስ የአንድ መፅሔት ዋጋ 11 ብር ከ99 ሳንቲም ነው። የአንድ መፅሐፍ ዋጋ ደግሞ ከ35 እስከ 60 ብር ድረስ ይሆናል። እናስ አቶ ግርማ ሆይ! እርስዎ ራስዎ መፅሐፍዎን እንደ መፅሔት 11 ብር ከ99 ሳንቲም እንዳልሸጡ እያወቁ፣ ምናለበት በጭፍን ጥላቻ ውስጥ ሆነው እንዲህ ዓይነት ውሸትን ባይጠቀሙ?…

በገሃድ የሚታወቅ እንዲህ ዓይነት ነገርን በግላጭ የሚዋሹን ከሆነ ነገስ “የሚፅፉት” ጉዳይ እውነት መሆኑን እንዴት ልናምን እንችላለን?...እጅግ ያሳዝናል፤ በጣምም ያሳፍራል። ለነገሩ ከሀገራችን የግል ሚዲያ ታሪክ እንደምንረዳው ሚዲያውን ለጥፋት የዳረጉት አብዛኛዎቹ ባልደረቦቹ ጋዜጠኛ ሳይሆኑ በፖለቲካዊ ስሜት ተገፋፍተው ያለሙያቸው ወደ ስራው የተቀላቀሉ ግለሰቦች ናቸው። አንዳንዶቹ የቀድሞው ስርዓት አባላት እንዲሁም ወታደሮች እንደነበሩ በዕድሜያችን ያየነው ዕውነታ ነው።

ገሚሶቹ ደግሞ ልክ እንደ አቶ ግርማ ያለ አንዳች ዕውቀት ሌጣ ፈረስ አገኘን ብለው ያለ ልጓም በሚዲያው ምህዳር ላይ የሚጋልቡ ናቸው። ለዚህም “ፋክት” እና መሰል መፅሔቶች ላይ ፈረቃ ገብተው የደፈና ጥላቻን የሚያራግቡ የአንድነትና የሌሎች የተቃውሞ ጎራ ባለሟሎችን ብቻ መጥቀስ ሃቁን የሚያሳይ ይመስለኛል። ታዲያ “ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል” እንዲል የሀገራችን ሰው በእነርሱው ብሶ የግል ሚዲያው ሁሌም የጋዜጠኝነት ስነ-ምግባርን እንዲሁም የሀገሪቱን ህግ ሳያከብር ውሸትን ብቻ እያራገበ መንቀሳቀሱን እንዲሁም አንድን ብሔር ከሌላው ጋር ለማጋጨት መጣሩ ብሎም የሀገሪቱን ህግና ስርዓት ተፃርሮ መስራቱን ይደግፋሉ።

ይህ ብቻ አይደለም። “ዘር ከልጓም ይጠቅሳል” እንደሚባለውም ይህን አሰራሩን እንደ ትክክለኛ አካሄድ በመቁጠር መልሰው “የግል ሚዲያው ህግና ስርዓትን ቢደፈጥጥ መንግስት ምን ያገባዋል?” እስከማለት ይደርሳሉ። ለኪራይ ሰብሳቢነትም ዋስና ጠበቃ ሆነው ይሞግታሉ። እናም እኔ እስከተረዳሁት ድረስ የተከበሩ አቶ ግርማ የማያውቁትን ሰነድ “ለመተንተን” የሞከሩበት ብሎም ስለሚዲያ አሰራር በውሉ ሳይገነዘቡ እዚህና እዚያ በመርገጥ ያቀረቡት “ፅሑፍ” ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ ይህን ዕውነታ የሚያንፀባርቅ ነው። ያም ሆነ ይህ ግን ለተከበሩ የፓርላማ አባል ሁለት ጥያቄዎችን አቅርቤ ፅሑፌን መቋጨት ወደድኩ።...አቶ ግርማ ሆይ! የህግ የበላይነትን የሚፃረር የግል ሚዲያ ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ጠቃሚ ነው ብለው ማሰብዎ አግባብነት አለውን?...የግል ሚዲያው ከህግ በላይ ሲሆን ዝም ተብሎ መታየት አለበትን?...